# የወያኔና የኢሠፓ ፀረ-ኢሕአፓነት፣ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ጥምረት

ከአብርሃም በየነ

“If falsehood like truth had but one face, we should know better where we are, for we should then take for certain the opposite of what the liar tells us. But the reverse of truth has thousand shapes and a boundless field.”

Montaigne

በዚህች ዓለም የሚኖሩ ነገሮች ሁሉ አርስ በርስ የተያያዙ ናቸው። ጨለማ ብርሃንን ተከትሎ ሲጓዝ ቀኝም በግራ ጎን ቆሞ እንደ ጥቁርና ነጭ አይነጣጠሉም። ዕውነትም ዕድሏ ሆኖ ከውሸት ጋር ተጓዳኝ ሆና ትኖራለች። ዳሩ የዕውነት መልክ አንድና አንድ ብቻ ሲሆን የተጓዳኟ የውሸት መልከ ግን ዥጉርጉርና ቅርፀ_ብዙ ነው። ውሸታሞችም ውሸታቸውን አሳማኝ ለማስመሰል እንደ አዳማጩ ዓይነት የውሸቶቻቸውን ቅርፆች እየቀያየሩ ሲዋሹ ከዕውነተኛው የተሻለ የማሳመን ማሳሂብ አግኝተው ብዙውን ጊዜ የመደመጥ ልቅናን ሲቀዳጁ ተስተውሏል። ለዚህም ነው ዓለም በውሸታሞች ከብራ የምትኖረው።

ሞንታኝ እንዳለው “ውሸት እንደ ዕውነት አንድ መልክ ቢኖራት ኖሮ ሁላችንም በተሻለ የዕውቀት ደረጃ ላይ ተገኝተን ውሸታሙ የሚነግረንን ተቃራኒ ለመቀበል እርግጠኞች እንሆን ነበር። ነገር ግን የውሸት ሺህ ቅርፅና ወሰን አልባ መሆን የውሸትን ተቃራኒ ለማመን እርግጠኞች እንዳንሆን አድርጎናል“። በመሆኑም ውሸታሞች ያልተባለን ተብሏል፣ ያልተደረገን ተደርጓል፣ ያልተሠራን ተሠርቷል፣ በማለት እንደ አዳማጮቻቸው ምኞትና ፍላጎት ውሸታቸውን ናኝተው ወደ አሳቻ መንገድ ይመራሉ። ሂትለርና እስታሊን በዚህ ዘይቤ በእጅጉ የተካኑ ዋሾና አንባገነን ነብሰ ገዳይ ገዥዎች ነበሩ።

ጆሴፍ እስታሊን ተቀነቀናቃኞቹን ለማጥፋት አበክሮ ይጠቀምበት የነበረው ዘዴ የባህሪይ ግድያን ነበር። ተቀናቃኞቹን በረቀቀ ውሸት በህዝብ ዘንድ አስጠልቶ በመጨረሻም ይረሽናቸው ነበር። ደርግም ያባቱ ልጅ እንዲሉ ተቃዋሚዎቹን የፍየል ወጠጤ እያስዘፈነ የመተረው ከስታሊን በቀዳው ዋሽቶ በመወንጀልና በቀይ ሽብር ጅምላ ጭፍጨፋ ነበር። በደርግ ዕግር የተተካው ወያኔ ግን ይህንኑ የውሸት ፋብሪካ ወርድና ስፋት ጨምሮ ከመገናኛ ብዙሃን የፕሮፖጋንዳ ፍጆታ በላይ በመፃህፍት ድጓስ ምዕራፍ ሰጥቶታል።

እስታሊን የተቀናቃኞቹን ቅልጥም ለመስበር የደራሲያን ማህበር መስርቶ ነበር። ይህ በአድርባዩ ስሜኖቭ ይመራ የነበረው የደራሲያን ማህበር የሶቬትን ህዝብ በሃሰት ወንጅሎ ወደ ሳይቤሪያና ኮሎማያ የማሰቃያ ጣቢያዎች አሰድዷል።ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ዜጎች በውሸት ወንጅሎ አስረሽናል። ፍርሃትም በአገሪቱ ግነቱ እጅግ እንዲንር አድርጎ ህዝቡ በደመነብሱ እስታሊንን እንደ ፈጣሪው እንዲያመልከው ህሊናውን ሰልቦት ነበር። እስታሊን ውሸቶቹ በህዝብ ዘንድ ሰርፀው እንዲገቡና ሰፊ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የፈጠራ ታሪኮችን ፈብርኮ አያሌ መፃህፍትን አሳትሟል። እነዚህ የውሸት ትረካዎች ግን ከእስታሊን ሞት በሁዋላ እሳት ዳር ያደረ እርጥብ ቆርበት በመሆን ደራሲዎቻቸውን አሳፍረው ወደ ቆሻሻ መጣያ ተጣሉ። በምትካቸውም አዳዲስ ድርሳናት በነሶልጀኒሲትን፡ ቫሲሊ ገሮስማንና በነ ቫርላም ሻላሞቭ ብዕሮች የእስታሊን ወንጀል በዓለም መድረክ እርቃኑን ቆመ።

ወያኔም እንደ እስታሊን ለባህሪይ ግድያ ባሰማራቸው ፀሃፊዎቹ ተራራውን ያንቀጠቀጠ ትውልድ፡ ጋሃዲ፡ ዕንዐት፡ ነበር፡ ምስክርነትና....... ሌሎችንም የሃሰት ትረካዎች አስተርኳል። ዳሩ የወያኔም የሃሰት ትረካ ነገ የኪወስክ የቡና መጠቅለያ እንደሚሆን ልብ ሊባል የገባዋል። የእስታሊን ጠላቶች ትሮትስኪና ተከታዮቹ ነበሩ። የደርግና የወያኔም ጠላት ኢ.ሕአፓ ነው። ግን ለምን ኢ.ሕአፓ?

ኢ.ሕአፓ ለደርግም ሆነ ለወያኔ አረመኔ ቡድኖች መስቅ የሆነው በህዝባዊነቱ እንጂ በሌላ ምክኒያት አይደለም። ስልጣን የህዝብ ብቸኛ ንብረት ነው፤ ስለሆነም ስልጣን ወደ ባለቤቱ እጅ መመለስ አለበት ብሎ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት እንዲቋቋም የደርግን ቡድን ታግሏል። ወያኔንም ገና ከበርሃ ቆይታው ጀምሮ የሽግግር መንግስት መመስረት እንደሚኖርበት ታግሎታል። እየታገለውም ነው። አምባገነኖቹ ቡድኖች ግን ያፀፋ መልስ የሰጡት ኢ.ሕአፓን በመግደል ነበር። ስለሆነም ኢ.ሕአፓነት በራሱ ወንጀል ሆኖ በቆመለት ዕናታዊ ዓላማው ተከሳሽ ሆኖ በደርግና በወያኔ በግፍ ተጨፈጨፈ። የዛሬው የኢሠፓና የወያኔ ፀረ-ኢ.ሕአፓነት መቀናጀም ምንጩ ይህ ነው።

እነዚህ ሁለት ፀረ_ህዝብ ሃይሎች በሰሩት ግፍና በፈፀሙት ወንጀል ነገ ተጠያቂ እንደሚሆኑ በመገመት ኢ.ሕአፓን ጨርሰው ለማጥፋት የጋራ ዘመቻ የያዙት ነገ ይህ ድርጅት ወደ ስልጣን ከመጣ በወንጀላችን ይፋረደናል ከሚል ፍራቻ መሆኑ ግልፅ ነው። ሌሎች ፀረ ኢ.ሕአፓ ግለሰቦችም ለዚሁ ዘመቻ በሚሊሻነት ለማገልገል የተቀጠሩ

አሉ። እንደ ዶ/ር  ዶ/ር ዓለም እሸቴ፡ ዶ/ር ሰላመ አብ፡ ዶ/ር አሰፋ ነጋሽ ፡ ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም፡ አቶ አሰፋ ጫቦ፡ ዶ/ር መሳይ ከበደ አቶ ገሞራው ካሳና መሰሎቻቸው በፀረ_ኢሕአፓ ዘመቻ ተሰልፈው ነበር። ብዙዎቹ የሚገባቸውን እየተቀበሉ ጥገ ጥግ ይዘው ተቀምጠዋል። እስካሁን ድረስ እንደቆሰለ አውሬ የሚቅነዠነዠው ግለሰብ ዶ/ር አሰፋ ነጋሽ ነው።

ውሃን ከጥሩው ነገርን ከስሩ ነውና አሰፋ ነጋሽ ማን ነበር? ብለን እንጠይቅ። ዶ/ር አሰፋ በሐረር ክ/ሀገር በሂርና ከተማ የተወለደ አብዮቱ የመጣበት የናጠጠ የፊውዳል ልጅ ነው። በነገራችን ላይ ሂርና ጓድ ጠናንና ግርማቸው ለማን ያፈራች ስፍራ ነች። የናት ሆድ ዥንጉርጉር ይሏል ይህ ነው። ወደ ተነሳንበት እንመለስና የአሰፋ አባት የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛ ነበሩ። በአፄው ዘመን የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛ መሆን ምን ያክል ስልጣን እንደነበረው አስቡት። ጭቃ ሹሙ ምስለኔውና አጥቢያ ዳኛው እንኳን ባቅሙ የመተያያ ሙክት፡ የእጅ መንሻ ዳውላ ማኛ ጤፍ፡ ማርና ቅቤ የገንዘብ ጉርሻና ሌላም ሌላም ከድሃው ባለ ጉዳይ ይጎርፍለት ነበር። ከፍ ያለ ስልጣን የነበራቸው ደግሞ ሰፋፊ የርሻ ማሳዎችና የከተማ ቦታ በገፍ ይዞታ ነበራቸው። ታዲያ አብዮቱ ይህን ሁሉ ዋጋ አሳጣው። ከፍ ብሎ ስማቸው የተጠቀሱት አብዛኛዎቹ አብዮቱ ሰለባ አደረገን ብለው የሚያምኑና በለውጡም መምጣት የሚቆጩ የሥርዓቱ ጥቅማጥቅም የተጓደለባቸው ግለሰቦች ናቸው።

ኢሕአፓንም የሚጠሉት ነቅናቂ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል ከሚል ቁጨት ተነስተው መሆኑ ግልፅ ነው። አብዮቱ በእርግጥም አሽቀልቁለው ይመለከቱት ከነበረው ህዝብ ጋር አኩል አሰልፏቸዋል። ይልቁንም ዛሬ ላይ ሆነው የትናንት ማንነታቸውን ዞር ብለው ሲመለከቱት ንዴታቸው ያመረቅዛል። ለዚህም ነው የለውጡን አቀጣጣይ ያን ትውልድ ጠምደው የያዙት። ከኢሕአፓ ጋር ጠባቸውም ይህ ነው። ባይሆንማ አገር ያፈረሰው ወያኔ ጠቀምጦ ኢሕአፓ በጠላትነት ባልተፈረጀና እንዲጠፋም ዘመቻ ባልተካሄደበት ነበር። የዶ/ር አሰፋ ትልቁ የንዴት ምንጭ ይህ ቢሆንም ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚሄድ ሌላም ምክኒያት አለው።

አሰፋ ነጋሽ በልጅነቱ ቅንዝንዝና ወኽባራ ነበር። ይህ የማይጨበጥ ባህሪው ያሳሰባቸው አባቱ አደብ ይገዛ ዘንድ ከህዝብ ት/ቤት አውጥተው በግል ት/ቤት በጴንጤ ፀሎት ቤት አስመዘገቡት። ብዙም ሳይቆይ አብዮቱ ፈነዳ። በወቅቱ የነበረው የለውጥ ሂደትም ወደነ አሰፋ ቤት አቅንቶ ሁኔታውን እንዳልነበር አደረገው። ወጀቡ ከድሃ በላይ ተመዘው እንደ

በርሃ ሽመል አገር አይብቃን ያሉትን ፊውዳሎች ቀድሞ አወዛወዘ። በዚህ ጊዜ አሰፋ ነጋሽ መስሎ ለመኖር በፍርሃት ነፋሱ ወደነፈሰው ሚዛኑን አይቶ ፊቱን ወደ ኢሕአፓ አዙሮ ድርጅቱን ተቀላቀለ። ኢሕአፓ በወቅቱ የደርግን የስልጣን ምሰሶ የነቀነቀበት ደርግም ተደናግጦ “ዲሞን በዲሞትፊር“ ባሉት መኢሶኖች መሪነት የጀምላ ግድያን ቀይ ሽብርን የጀመረበት ወቅት ነበር።

የአሰፋ አባትም ልጃቸው የቀይ ሽብር ሰለባ ከመሆኑ በፊት ገለል ሊያደርጉት ፈለጉና የሚያውቁትን ባለስልጣን አፈላልገው አሰፋን ወደ ኩባ ላኩት። ዶ/ር አሰፋም በካድሬነት ደርግን ለማገልገል ስልጠናውን ቀጠለ። በዚህ መሃል የደርግ ስልጣን በመሪው ፍርጠጣ ተጨመጨመ። ዶ/ር አሰፋም ከኩባ ወደ አውሮፓ በስደተኝነት ተሸጋገረ። የሰለጠነበትን የካድሬነት ሙያ ሳይፈትነውም ወያኔ የሚኒሊክን ቤተ መንግስት ተቆጣጠረው። አሰፋ ሁለት ሞት ሞተ። አንድ ያባቱን ንብረት አብዮቱ ቀማው። ሁለት በካድሬነት ስልጣን ተቆናጦ አዛዥ ናዛዥ ሊሆን አልሞት የነበረው ምኞቱ በደርግ ውድቀት መክነ። ዶ/ር አሰፋም ወያኔ ይህን ያክል ጊዜ ይገዛል ብሎ ስላላሰበ በደም ፍላት በወያኔ ላይ መፅሀፍ ፃፈ። በዚህ መልክ የአሰፋ ነጋሽ ወደ አገርቤት መመለስ ህልምና ቅዠት እየሆነ ተፈራረቀ። ዶ/ር አሰፋም ለዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ተጠየቂ ኢሕአፓን ማድረግ ፈልጎ በወያኔ ሚልሻነት ኢሕአፓን ለማጥቃት ተሰልፎ ተንቀሳቀሰ።

የዶ/ሩ ከወያኔ ጎን መቆም የቂም ቁርሾ መሆኑ ቢገባንም በሌላ በኩል ግን ዶ/ር አሰፋን የሚያሳስበው ነገር መኖሩ ግልፅ ሊሆንልን ይገባል። ዶ/ር አሰፋ ባለህልም ነው። ይህንንም ህልሙን ዕውን ለማድረግ ቀደም ሲል የመኢሐድ፡ በሁዋላም የኮ/ል ጎሹ ወልዴ፡ ቀጥሎም የኢዴፓ አያይዞም የቅንጅት ዛሬ ደግሞ የመኢአድ ደጋፊ በመሆን ማንም ያገኘ ድርጅት የሚያሽከረምመው የፖለቲካ ጋለሞታ ሆኖ ኖሯል። ይህ ሁሉ እንደ አብሽሎ መገለባበጥ ደግሞ ዶሮ ለብልሃቷ ተንጋላ ትጠጣለች እንዲሉ ቀድሞ ወደ ስልጣን ለመውጣት እድሉ የገጠመው ድርጅት ኩርማን ስልጣን አይነሳኝ ይሆናል ከሚል ምኞት የመነጨ ነው።

ስለሆነም የኩርማን ስልጣን ተስፈኛው ዶ/ር አሰፋ እነዚህ ሃይሎች ስልጣን ከመጨበጣቸው በፊት ኢሕአፓ ስልጣን እንዳይዝ ሌት ተቀን ይፋትራል። ኢሕአፓንም የተውሶ ፍልስፍና ወደ አገር አስገባ ብሎ ይወነጅላል። ኣላወቀውም አንጂ የውጭ ባህልና ፍልስፍና መግባት የጀመረው ባዔው ዘመን ነበር። ደጃዝማች፣ ግራዝማች፣ ፊታውራሪ...... ወዘተ የመሳሰሉት የውትድርና ማእረጎች ተለውጠው ኮሎኔል፣ ጀኔራል፣

ሻለቃ……ወዘተ በሚሉ የውጭ ማእረጎች የተተኩት ባዬው መንግስት ዘመን ነበር። ለነገሩ ካፒታሊዝምና ሊበራል ዲሞክራሲም አገር በቀል አለመሆናቸውን የኩባው ካድሬ ሊገነዘብ አልቻለም። ዶ/ር አሰፋ ነጋሽ እንደካድሬነቱ ፕሮፖጋንዳ ከመንዛት በመለስ የነገሮችን እድገት ከዓለምና ከአገር አቀፍ ተጨባጭ ሁኔተዎች ጋር ለመመርመር የፖለቲካ ክህሎቱ የብቅል ዱቄት ያክል ነው። ለዚህም ነው የተማሪው ንቅናቄ ለምን ወደ ምስረቅ ፊቱን አዞረ? ብሎ እሚጂርቀው። ንጉሡ ለምዕራቡ ዓለም ጋሻ ጃግሬ በነበሩበት ዘመን፣ በርካታ የ አፍሪቃ አገሮች በምዕራባዊያን ቅኝ ግዛት ስር በነበሩበት ወቅት፤ የሶስተኛ ዓለም አገሮች ከቀጥታና ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት ሲፋለሙ በቦቃ ሳት አናር ይነዱ በነበረበት ዓለማቀፋዊ ሁኔታ ወደ አሜሪካ ፊት ሊዞር የሚታሰብ አልነበረም። ዳሩ እነዚህንና ሌሎች ብዥታዎቹን በመድረክ ለማወያየት በ25ኛው የልደት በዓሉ ኢሕአፓ ዶ/ር አሰፋን ጋብዞት ነበር። ነገር ግን ይህ ወኔ የከዳው ካድሬ የተሰጠውን የመድረክ ጊዜ ስለፃፈው መፅሃፍ ማስታወቂያ ተናግሮበት ተቀመጠ።

እርሱ የለመደው ከመጋረጃ በስተጀርባ ፕሮፖጋንዳ የመንዛት ባህሪይ ከኢሕአፓ የመድረክ ውይይት ባህል ጋር ፊፅሞ ሊገናኝ ባለመቻሉ ወደ ለመደው በሩቅ እርቀት ስም ወደ ማጥፋቱ ስምሪት ተሰማራ። በዘህም ስምሪቱ በሰሞኑ ደርጎች ተሰባስበው በደም የዋጁ ታሪካቸውን በኢሕአፓ ለማላከክ የፃፉትን "ምስክርነት" የተሰኘ መፅሐፍ እፁብ ድንቅ ሥራ ብሎ ገምግሞታል። ከዚሁ "ምስክርነት" ከተሰኘው የውሸት ትረካ በ7ኛው ገፅ ከሰፈረው የውሸት ዝክንትል በቅንጭፉ አንድ ዘለላ ልምዘዝ።

"ከዚህ በፊት በኢሕአፓ ተንኳሽነት የተቀሰቀሰው የመንገድ ላይ ግድያ(የመንገድ ላይ ግድያ የመጀመሪያ ዒላማ ፈረንሳይ አገር የተማረው ዶ/ር ፍቅሬ መርዕድ ነበር። ፍቅ ሬን የገደሉት 1. መምህር በላይ ገብረማሪያም ቡልጋሪያ ሁለት ዓመት ተምሮ የተመለሰ ………..ለሽፋንም ቃሊቲ ዶሮ ርባታ አካሂዳለሁ በማለት ለኢሕአፓ መደራጃ ቦታ አዘጋጅቶ የነበረ፣ ተኩሶ የገደለና 2. ይትባረክ ሕዝቂያስ የ24 ዓመት ወጣት ከአሜሪካ በፖለቲካል ሳይንስ ቢ.ኤ. የነበረው የቀይ ቮልስዋገን አውቶሞቢል ሾፌር ሆኖ ነው ግድያ የፈፀሙት።) የጥቅሱ መጨረሻ።

"……በኢሕአፓ ተንኳሽነት የተቀሰቀሰው የመንገድ ላይ ግድያ" የምትለዋን ሀረግ ልብ በሏት። "የመንገድ ላይ ግድያ የመጀመሪያ ኢላማ…" ( ሰረዝ የተጨመረ) ከምትለው ሀረግ ጋር በኑባቤ ተጣመራ የምትሰጠው ትርጉም የመንገድ ላይ ግድያን በመጀመሪያ የጀመረው ደርግ እንደነበር ነው የሚገልፀው። የፍቅሬ መርዕድ ሞት ቀደም ሲል በራሱ

በደርግ መንገድ ላይ መግደል ተጀምሮ ግን ጋብ ብሎ የነበረውን የመንገድ ላይ ግድያ የፍቅሬ ሞት ቀሽቃሽ ነበር ማለት ነው። ይህ አባባል ኢሕአፓ የግድያ ጀማሪ እንዳልነበር ያስረዳል። የደርጉ መርማሪ ሻ/ል ተስፋዬ ርስቴ ገና መፅሃፉን "ሀ" ብሎ ሲጀምር በዚህ መልክ የውሸት ታሪኩ አየፈተለከ እስከ መጨረሻው ገፅ ይዘልቃል።

በመጀመሪያ መምህር በላይነህ የበዕደ ማርያም ት/ቤት ተማሪ ነበር። ከበዕደማርያም ውጥቶ በነቪ የጦር ክፍል ተመዝግቦ ስልጠና ላይ እንዳለ ጠፍቶ ወጣና በመምህርነት ሙያ ተሰማራ። ሻ/ል ተስፋዬ ርስቴ እንደሚዋሸው ቡልጋሪያ በላይነህን አታውቀውም። እርሱም አያውቃትም። የቀይዋ ቮልስዋገን ሾፌር የነበረውም በአሚሪካ የቢ.ኤ ዲግሪ የነበረው ግለሰብ አልነበረም። የአዲስ አበባ ኗሪና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ የነበረ ለላ ነው። የሆነ ሀኖ ግን ታሪኩ ዕውነትነት ይጎድለዋል። የዶ/ር አሰፋም አዳናቂ ግምገማም እንደ ድርሰቱ በውሸት ላይ የተመረኮዘ ግም ግምገማ ነው።

መስከረም 2002 ዓ.ም.

እንኳን ለዘመን መለወጫ አደረሳችሁ!!!